# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም።

ልዩ እትም 3/1/67


## የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ትግል ይቀጥላል

የግፈኛውና የወንጀለኛው የሃይለስላሴ ከስልጣን መወገድ ባለፈው የካቲት ወር ለፈነዳ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴ ታላቅ ድል ነው። ሰፊው ሕዝብ በዚህ በተቀዳጀው ድ በመበረታታት ለዲሞክራሲና ለኑሮው መሻሻል የጀመረውን ትግል ከግቡ ሳያደርስ ከቶ ወደ ኋላ አይል

ደርጉ በበሰበሰው የአስተዳደር ስርአት ፈላጭ ቆራጭ በሃይለስላሴና በአገልጋዮቹ ላይ የወሰደው ታሪካዊ እርምጃ የሕዝቡን ጥያቄና ፍላጎት ስለሚከተል በእርግጥ የሚደገፍ ነው። ሆኖም፡—

1. የሕዝቡን የበላይነትና የሕዝቡን የስልጣን ምንጭነት በመቀበል የሕዝብ መንግስት/ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ/ አለማወጁና፡ለአገሪቱዋ ውድቀት፡ለሕዝቡ መከፋፈል ዋና ምክንያት የሆነው ዘውድ አለማስወገዱ።

2. በጊዜያዊ መልክም ቢሆን የሰፊውን ሕዝብ እውነተኛ ወኪሎች ሳይጨምር የመንግስቱን ስልጣን ለብቻው መያዙ የሕዝቡን ፍላጎትና ጥያቄ የሚፃረር መሆኑ የማያጠራጥር ነው።

የሃይለስላሴ ባላባታዊ መንግስት ገበረአበርና የበላይ ጠባቂ የነበረው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በስለላ ድርጅቱ በሲአይኤ በኩል በደርጉ አካባቢ ጉድጉድ ሲል በመሰንበቱ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እጅ እንዳይኖር ያሰጋል።

እዚህ የደረሰው የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል መጨናገፍ የለበትም። ስለዚህ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲና ለኑሮ መሻሻል የጀመረውን ትግል በበለጠ ሃይል መቀጠል አለበት። ይገባዋልም። ትግሉ ሳይበርድ በሚከተለው አኳሃን መቀጠልና መፋፋም ይገባዋል፡—

1. በየመስሪያ ቤቱ፡በየፋብሪካው፡በየሙያው፡በየሰፈሩ፡በየእድሩ፡በየቀበሌው በሚቻልበት መንገድ ሁሉ ሰፊው ሕዝብ ኮሚቴዎች እንዲያቋቁምና እንዲደራጅ። ከዚህ በፊት ያሉትንም ድርጅቶች እንዲያጠነክር። እነዚህንም በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚያገናኙ አጠቃላይ ኮሚቴዎች በማቋቋም ህብረቱንና አንድነቱን እንዲያጠነክር።

2. ለሙሉ ዲሞክራሲና ለኑሮው መሻሻል የትግሉ እንቅስቃሴ መነሾ የሆኑትን ጥያቄዎችን በመልክ በመልካቸው አድርጎ እንደሚከተለው ይዞ እንዲቀርብና እንዲታገል ያስፈልጋል፡—

ሀ/ ከሰፊው ሕዝብ በምርጫ የተውጣጡ ወኪሎች ያሉበት ጊዜያዊ የሕዝብ መንግስት አሁኑኑ እንዲቋቋም።

ለ/ ሰባዊና ብሄራዊ መብቶችና ነፃነቶች፡በተለይ የጋዜጣ፡የማህበር፡የመሰብሰብ መብ አሁኑኑ እንዲረጋገጡና ስራ ላይ እንዲውሉ።

ሐ/ እስከሶስት ወር ድረስ አዲስ ሕገመንግስት ተዘጋጅቶ ሙሉ ዲሞክራሲያዊ የሕዝብ መንግስት እንዲቋቋም።

መ/ ሃይለስላሴ ከነቤተሰቡና ከነገበረአበሮቹ ታስሮ ለፍርድ እንዲቀርብ። እርሱ ገብረአበሮቹ የአጋበሱት የሕዝብ ሃብት በሙሉ እንዲወረስና ለሕዝብ እንዲገባ።

ሠ/ በመሳሪያነትና በገብረአበርነት ሕዝቡን የበደሉ፡የዘረፉና የጨቆኑ፡አሁን በከፍ ስልጣን ላይ ያሉት ብዙዎቹ ባለስልጣኖች ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡና ንብረታቸውም እንዲወረስ።

ረ/ መሬት ላራሹ፡ለስራአጡ ስራ፡ለሰራተኛው ሃቀኛ የጉልበት ዋጋውን፡ለረሀብተኛው እህልና ውሃ ወዘተ. እንዲደርሰው አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ።

.....2

እነዚህና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በቶሎ መልስ እስኪያገኙ ድረስ በትጋት መታገል አለ
የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ! ብዝበዛን ግፍን በደልን በመቋቋም ደምህን አፍስሰህ አጥ-
ህን ከሰከሰህ ያደረግከው ከባድ ትግል ያለፍሬ መቅረት የለበትም፤ አይገባምም:: ትግሉን ማ
ሚያ ጊዜ አሁን ነው:: ለአሁኑ የኢትዮጵያ ችግር መፍትሄው ወታደራዊ መንግስት ሳይሆን የሕ
ሕዝብ መንግስት መቋቋም ነው:: 'አባት ካለ አጊጥ፡ጀንበር ካለ እሩጥ' የሚለውን እውነት
በመከተል ትግሉን መቀጠል አሁን ሁኔታው ሳይበርድ ነው:: ተጥቀህን አጥብቀህ ትግሉን ወደፊት
መግፋት አለብህ:: ህብረትህንና አንድነትህን በቆራጥነት ገንብተህ ትግሉን ሙሉ ዲሞክራሲያዊ
መንግስት ወይም ሞት በሚል ከፍተኛ ጥሪ መምራት አለብህ::

ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚደረገው ትግል ያሸንፋል::
ባንድነት በቆራጥነት እንታገል::
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::